□ት ሬ □ □ አ ስ ተ □ □ ር

ት ሬ ነ □ ሪ ት □ □ □

# DIRE NEGARIT GAZETA

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

| 5ኛ ዓመት ቁጥር 003<br>ትሬ□□ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፳፻፲ | በትሬ□□ አስተ□□ር<br>ምክር ቤት □ባቂነት □□□ | 5th Year No. 003<br>DIRE DAWA 2nd NOVEMBER,2017 |
|---|---|---|

## አዋጅ ቁጥር ፶፮/፳፻፲

## የድሬደዋ አስተዳደር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ በተነደፈው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በብዛት እንዲፈጠሩ ለማስቻል የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የእሴት ሰንሰለት መሠረት ያደረገ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

## PROCLAMATION NO. 56/2017

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION SMALL AND MEDIUM MANUFACTURING INDUSTRY CLUSTER DEVELOPMENT CORPORATION.

**WHEREAS**, it is found to provide support for industries in the small and medium scale manufacturing sector based on the value chain to create numerous manufacturing industries in accordance with the promulgated economic policy and strategy so as to bring our country among the countries that have middle income ;

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላትን ውጤታማ በሆነ መንገድ በማልማት፣ በማስተላለፍና በማስተዳደር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎቹ በቅንጅት እንዲሁም በውድድር መንፈስ እንዲሰሩ የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተለያዩ ጊዜያት በአስተዳደሩ የተገነቡ የማምረቻ ማሳያና መሸጫ ህንፃውዎችና ሼዶች አግባብና ሥርኣት ባለው መንገድ ማስተዳደር በማስፈለጉ፤እና ይህንንም ተግባር የሚያከናውን ራሱን የቻለ የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት በህግ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የድሬደዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬደዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ?፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) (በ) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የድሬደዋ አስተዳደር አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፶፮/፳፻፲ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**WHEREAS**, it is found necessary to create a structure and establishes a procedure for manufacturing industries in order to enable them to work in a cooperation and competitively so as to develop, transfer and administer manufacturing industry cluster centers in an effect way;

**WHEREAS**, it is found necessary to establish a public enterprise legally, which will be engaged in properly administering the manufacturing, display, selling buildings and shades built by the administration in different times;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 12 sub –article (1) (a) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No.416/2004, the Dire Dawa Administration councel, is hereby proclaimed as followes.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as " the establishment of small and medium manufacturing Industry cluster development corporation of Dire Dawa Administration proclamation N0. 56 /2017".

## ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ **"አስተዳደር "** ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፤

፪ **"ኮርፖሬሽን"** ማለት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል በዚህ አዋጅ መሠረት ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ ህጋዊ ሰውነት ያለው አንድ የኢኮኖሚ ድርጅት ነው፤

፫ **"ቢሮ"** ማለት የድሬደዋ አስተዳደር ንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ነው፤

፬ **"ቦርድ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተቋቋመ የኮርፖሬሽኑ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

፭ **"ኢንዱስትሪ"** ማለት በአብዛኛው በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስና በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ የማምረቻ፣ የማቀነባበሪያና መገጣጠሚያ ድርጅት ነው፤

፮ **"ክላስተር"** ማለት በአንድ አካባቢ ሆነው ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ የእሴት ሰንሰለት ጠብቀው የሚያመርቱ አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙበት ማዕከል ነው፤

## 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

1. **"Administration"** means the Dire Dawa Administration;
2. **''Corporation''** means an economic organization which is legally established under this proclamation with a profit generation motive so as to serve the purpose of implementing this proclamation;
3. **" Bureau"** means the Dire Dawa Administation Trade Industry and Investment Bureau;
4. **''Board''** means the management board of the corporation formed in accordance with Article 6(2) of this proclamation;
5. "**Industry**" means a higher or medium level manufacturing, combining and assembly organization which mostly works using motor power;
6. "**Cluster**" means a center in which small and medium manufacturing industries are found in one area and produce in an integrated manner through keeping the value chain;

፯. **"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ"** ማለት የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ፮ እስከ ፴ ሰዎችን የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ 1,500,00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) የሆነ ኢንዱስትሪ ነው፤

7. "**Small manufacturing Industry**" means an industry having a total capital, excluding building, froa Birr 100,00 to Birr 1,500,000 ( one Hundred thousand one Birr to one million five Hundred thousand Birr) in manufacturing sector and engages from 6 to 30 workers including the owner, his family members and other employess;

፰. **"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ"** ማለት የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ፴፩ እስከ ፻ ሰዎችን የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ከብር ህንፃን ሳይጨምር 1,500,001 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ አንድ ብር) እስከ 20,000,000 (ሃያ ሚሊዮን ብር) የሆነ ኢንዱስትሪ ነው፤

8. "**Medium manufacturing Industry**" means an industry having a total capital, excluding building, from Birr 1,500,001 to birr 20,000,000 (one million five hundred thousand one Birr to twenty million birr) in the manufacturing sector and engages from 31 to 100 workers including the owner, his family members and other employees;

፱. **"ማምረቻ"** ማለት ደረጃውን በጠበቀ ማቴሪያል ከG+0 ጀምሮ የሚገነቡና ለአነስተኛና ለመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርት ማምረቻና መሸጫ አገልግሎት የሚውሉ ሕንፃዎች ናቸው፤

9. "**Manufacturing**" means buildings which are constructed, starting from G+0, in a standard material and used for the purpose of producing and selling the products of small and medium manufacturing industries;

?.“**የኢንዱስትሪ ዞን**” ማለት በአስተዳደሩ ከተማ ፕላን መሰረት ለኢንዱስትሪ የተከለለ ቦታ ነው፤

?፩.“**የኢንዱስትሪ ብክለት**” ማለት በማምረቻና አገልግሎት በመስጠት ሂደት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በክላስተር ማዕከላቱ አካባቢ የሚፈጥሩት ለሰው ልጅ አመቺ ያልሆነና ለጤና ጠንቅ የሆነ የቆሻሻ፣ የድምጽ እና አየር ብክለት ነው፤

?፪.“**ጠቅላላ ንብረት**” ማለት የኮርፖሬሽኑ የማይንቀሳቀስና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች፣ ኮርፖሬሽኑ ገና ያልተቀበላቸው ገቢዎች፣ ጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሲሆን ግዙፍ ያልሆኑ ንብረቶችን፣ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችንና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸው ሂሳቦችን ይጨምራል፤

?፫.“**የተጣራ ጠቅላላ ንብረት**” ማለት ከጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘው የሂሳብ ዓመት ውስጥ የሚከፈሉ እዳዎች፣ በረጅም ጊዜ የሚከፈሉ እዳዎች፣ በቅድሚያ የተከፈለ ገቢና ሌሎች እዳዎች ተቀንሰው የሚቀረው ንብረት ነው፤

?፬.“**ካፒታል**” ማለት ኮርፖሬሽኑ በተቋቋመ ጊዜና ከዚያም በኋላ በአስተዳደሩ የሚመደብ የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፤

10. “**Industry Zone**” means a demarcated area for the industry, according to the urban plan of the Administration;
11. “**Industry Pollution**” means a waste sound or air pollution that is inconvenient for the human being and harmful to health which is produced in the areas of the cluster centers in the production and service rendering process of the small and medium manufacturing industries;
12. “**Gross Asset**” means movable assets, fixed assets, payables, receivables, cash and bank account of the corporation including intangible properties pre-paid expanses and incomes to be collected;
13. **“Net Asset”** means a balance after the payment of loans to be paid within the fiscal years, long term loans, earnests, and deduction of all payables;
14. **“Capital”** means a value of initial money and additional budget allocated and net asset after the establishment of the corporation;

?፭.**“የተጣራ ትርፍ”** ማለት ልዩ ልዩ ወጪዎችና ታክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሳብ ነው፤

?፮.**“የመንግስት የትርፍ ድርሻ”** ማለት ኮሮፖሬሽኑ ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ገቢ የሚሆነው ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረው ሂሳብ ነው፤

?፯.**“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

?፰.ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

**፫ <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በድሬደዋ አስተዳደር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪነግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፖሬሽን፣ በኮሮፖሬሽን አመራር እና ሠራተኞች እንዲሁም በቦርድ አባላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መቋቋም፣አላማ፣ አደረጃጀት እና ሥልጣንና ተግባር</u>

**፬ <u>መቋቋም</u>**

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮሮፖሬሽን (ከዚህ በኋላ “ኮሮፖሬሽን” እየተባለ የሚጠራ) የድሬደዋ አስተዳደር የመንግሥት ልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

15. **“Net profit”** means a balance after deduction of all expenses and income tax;
16. **“Government Dividend”** means a balance after deduction of legal reserve and other reserve from the net profit;
17. **“ Person”** means any natural or juridical person;
18. any expression in the masculine gender includes feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This proclamation shall be applicable in Dire Dawa Administration small and medium manufacturing industry cluster development corporation management, employees and board members of the same.

## <u>PART TWO</u>

## <u>ESTABLISHMENT, OBJECTIVES, ORGANIZATION AND POWER AND DUTIES.</u>

**4. <u>Establishment</u>**

The small and medium manufacturing industry cluster development corporation (hereinafter the “corporation”) is hereby established as Dire Dawa Administration public enterprise.

፭. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

ቢሮው የኮሮፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

፮. ዓላማ

ኮሮፖሬሽን የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ ከሚመለከታቸወው አካላት ጋር በመሆን የአስተዳደሩን የከተማ ፕላን መሰረት ያደረገ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ማካሄድ የሚያስችል የተቀናጀ የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ።

፪ የአነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ስራው ደረጃውን በጠበቀ የክላስተር ማዕከላት ግንባታ ዲዛይን እንዲለማ፤ ወጥንት ኢንዲኖረው፤ እና ከሚለማው ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ጋር የሚጣጣም ሆኖ እንዲገነባ ማድረግ፡፡

፫ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የእርስ በእርስ ክህሎትና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ተገቢውን አደረጃጀት እንዲሁም አሰራር በመዘርጋት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው በቅንጅት እና በውድድር መንፈስ እንዲሰራ ማስቻል።

፬ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለልማታዊ ባለሃብቶች በክላስተር የለማ የማምረቻ ቦታ በኪራይ በማቅረብ ኢንዱስትሪዎች የነበረባቸውን የለማ የማምረቻ ቦታ እጥረት እና ላልተገባ አላማ ይውል የነበረውን የመሬት አጠቃቀም ችግር መቅረፍ፡፡

5. Supervising Authority

The Bureau shall be the supervising authority over the corporation.

6. Objectives

The following are founding objectives of the corporation:

1. In corporation with concerned bodies, shall cause the existence of integrated land and infrastructure supply that could enable to undertake small and medium manufacturing industry cluster development according to the urban plan of the city.
2. Shall cause the consecution of small and medium manufacturing industry development to be aligned with standardized cluster's center building designs, shall be consistent and compatible with the manufacturing industries to be developed.
3. Shall enable the manufacturing industry to work in cooperation and in a competitive manner though establishing organizations and operational arrangements so as to create self-skill and market linkages within the manufacturing industry.
4. Shall resolve the prevailing problems of industries pertinent to shortage of devloped land, mis oppropriated use of land through providing cluster based developed manufacturing places with lease arrangement for development investor of the manufacturing industry.

፭ ቀደም ሲል በከተማ ስራ ዕድል ፈጣራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ የተገነቡ የማምረቻና መሸጫ ክላስተር ማዕከላትን በመረከብ አስፈላጊው ጥገና እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ በማካሄድ ለተገነባለት አላማ አገልግሎት እንዲውል ማስቻል፡፡

## ፯ አደረጃጀት፣

ኮርፖሬሽኑ የሚከተለዉ አደረጃጀት ይኖረዋል፦

፩ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

፪ የሥራ አመራር ቦርድ ( ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፫ ዋና ስራ አስኪያጅ፣

፬ ሌሎች የሥራ ክፍሎች እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰ የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር

፩ የቦርድ አባላትን ለአስተዳደሩ ካቢኔ አቅርቦ ያሾማል፤

፪ ለቦርድ አባላት ሊከፈል የሚገባውን አበል ይወስናል፤

፫ የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፤

፬ የኮርፖሬሽኑን መነሻ ካፒታል ከአስተዳደሩ ያስመድባል፤

፭ የኮርፖሬሽኑ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ይወስናል፤

5. Shall receive the manufacturing and marketing cluster centers built preveously by Urban Food Security and Employment Creation Agency; carry out the maintenance and improvement of the same accordingly, cause it service for the predetermined objective.

## 7. Organization

The corporation shall have the following organization:

1. Supervising Authority;
2. Management board (Hereinafter ``Board``);
3. General manager; and
4. The other necessary departments and staffs required for the job.

## 8. Powers and Duties of the supervising Authority

1. cause the appointment of board members by the administration cabinet;
2. determine the amount of allowance that should be paid for board members;
3. shall assign externals auditors;
4. cause the allocation of initial capital of the corporation by the administration;
5. decide the increase or decrease of the capital of the corporation;

፮ ከቦርዱ በሚቀርብለት ሀሳብ መሠረት ከተጣራው ትርፍ ውስጥ በየዓመቱ ለመንግስት ፈሰስ ሊደረግ የሚገባውን የገንዘብ መጠን ይወስናል፤

፯ የኮሮፖሬሽኑን የሂሳብ ሪፖርትና የውጭ ኦዲት ሪፖርት ያፀድቃል፤

፰ በቦርዱ የሚቀርብለትን የኮሮፖሬሽኑን የኢንቨስትመንት እቅድ ያፀድቃል፤

፱ ከቦርዱ ጋር በመመካከር የኮሮፖሬሽኑን ዓመታዊና አጠቃላይ ግቦችን ያፀድቃል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

? ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት የባለቤትነት መብትን ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፱ **የኮሮፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር**

ኮሮፖሬሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግበራት ይኖሩታል፡-

፩ የተሟላ መሰረተ ልማት የተዘረጋላቸው የማምረቻ፣ የመሸጫና ምርት ማሳያ ቦታዎችን በክላስተር ማዕከላት በመገንባት የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በኪራይ ያስተላልፋል፣ ኪራዩንም ይሰበስባል፣ ያስተዳድራል፤

6. determine, based on the proposals of the board, the amount of state dividend to be paid to the Government from the net profits of each financial year;
7. approved the financial report and external audit report of the corporation;
8. approved the investment plan of the corporation presented by the board;
9. approved the annual general goals of the corporation,jointly with the board; follow up the execution of the same;
10. Without prejudice to the powers and duties vested to the board, undertake other activities relevant to secure the Government owenership rights.

9. **Powers and Duties of the Corporation**

The corporation shall have the following power and duties:

1. build manufacturing, selling and production display places which have complete infrastructural facilities in the cluster centers and transfer it through lease to small and medium manufacturing industries, collect the rent; and administer the same;

፪ በአስተዳደሩ የሚገኙ ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ፣ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ እንዲሁም በከተማ ስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ አማካይነት በግንባታ ላይ የሚገኙ ነባር የማምረቻ፣ የመሸጫና ምርት ማሳያ ህንፃዎችን በመረከብ አስፈላጊውን ማስተካከያና ማሟያ አድርጎ ያስተዳድራል፤

2. receive and administer existing manufacturing places and manufacturing,selling and production display places found in the administration which are operational, non operational and those which under construction, by the urban food security and Employment creation Agency;

፫ የክላስተር ማዕከላት ልማት ከኢንዱስትሪ ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ መሆኑን በየጊዜው ያረጋግጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱ በመፈተሽ እንዲከለስ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

3. ensure the cluster centers development is consistent and up to date with industrial policy periodically; exmanine and present decision idia accordingly;

፬ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለክላስተር ማዕከላት ማስፋፊያ ግንባታ አገልግሎት የሚውል የለማ መሬት እንዲዘጋጅ እና በቂ በጀት እንዲመደብ ያደርጋል፡

4. cause the preparation of developed land and the allocation of adequate budget for the purpose of building expansions of cluster centers together with the concerned organs;

፭ በክለስተር ማዕከላት ውስጥ መሰረተ ልማትን ያሟላል፤

5. fulfill infrastructures in the cluster centers;

፮ ከአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ ተለይተው የሚቀርቡለትን የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አንቀሳቃሶችን በክላስተር ማዕከላት ያደራጃል ፤ እርስ በርሳቸው ወይም ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በቴክኖሎጂ በገበያ እንዲተሳሰሩ ያደርጋል፤

6. organize small and medium manufacturing industries operation that are identified by the small and medium manufacturing industry development agency in cluster centers; cause them to creat linkage with each other and with higher industries with technology or market;

፯. ለክላስተር ማዕከላት ግንባታ የሚውል መሬት በመረከብ ደረጃውን የጠበቀ ከአስተዳደሩ እድገት ጋር የተገናዘበ እና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የግንባታ ዲዛይን እንዲዘጋጅና ግልፅ ጨረታ በማውጣት ግንባታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የግንባታ ጥራትን ይከታተላል፤ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤

7. recive a land for the purpose of cluster centers construction, and cause the preparation of a design which is standardized, in harmony with the development of the administration and takes the objective condition of the area into consideration and carry out the construction through open tender, follow up the performance of the same;

፰. በክላስተር ልማቱ ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፤ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

8. identify problems which are encountered in the cluster development; cause to carry out environmental impact assessment; coordinate and lead the same;

፱. የክላስተር ማዕከላትን በሚመለከት በተለዩ በችግሮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ዉሳኔዉ ተግባራዊ እንዲሆን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤ ያስፈፅማል።

9. facilitate conditions to set a solution frame work on the identified problems in the area of cluster centers through stakeholders platform; follow-up, coordinate and implement the decision;

?.የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የፋይናንስና የቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ይደግፋል፤

10. design and support a procedural system for accessing financial and technological input supply for small and medium manufacturing industries;

?፩.የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከአገር ውስጥ ምርት የጥሬ ዕቃ እና ለምርታቸውም የውጪ ገበያ ትስስር የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ይደግፋል፤

11. design and support a procedural system for small and medium manufacturing industries to access them raw materials locally and facilitate foreign market linkage for their product;

?፪.ለጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውጪ ላሉ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻና የመሸጫ ቦታ ለመገንባት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በሚይዘው እቅድና በጀት መሠረት እንዲገነባ ያደርጋል፤

?፫.የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት የማግኘት፣ ባለይዞታና ባለቤት የመሆን፣ የማስተላለፍና በመያዣነት የመስጠት መብት ይኖረዋል፣ውል ይዋዋላል፤

?፬. የባንክ ሂሳብ፣ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

?፭.እንደአስፈላጊነቱ ለስራው አመቺ እንዲሆን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ያቋቁማል፤

?፮.ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

12. undertake construction of production and marketing places accordingly, for micro and small scale enterprises other than the manufacturing sector, in accordance with the plan and budget allocated by Dire Dawa administration Urban Food Security and Employment Creation Agency ;

13. shall have the right to obtain real mobile property ; have the right to title dead and owenership, to transfer and provide as a collateral of the same; enter into agreement;

14. open bank account and operate the same;

15. establish branch offices accordingly so as to make its operation accessible;

16. undertake other activities necessarily to achieve its objective.

**? <u>የቦርድ አመሰራረት</u>**

፩ የቦርድ አባላት ቁጥር አስራ ሁለት ይሆናል፡፡

፪ የቦርድ አባላት በአስተዳደሩ ከንቲባ ይሰየማሉ፡፡

፫ የቦርድ አባላት ምደባና ምርጫ የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች ያካተተ እንዲሁም የሌሎች አካላት ምደባና ምርጫ በሙያ፣ በስራ ልምድና በችሎታ ብቃት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤

**10. <u>Establishment of management Board</u>**

1. The number of members of the board shall be twelve.
2. The board members shall be appointed by the administration mayor.
3. The appointment and nomination of board members shall consists the representation of public officials, the assignmet and nomination of other bodies will be based on professions, expeience and ability.

፬ የቦርድ አባላት የስራ ጊዜ አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል የሥራ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሥራ ሊመደብ ወይም ሊመረጥ ይችላል፤

፭ የቦርድ የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የአባላቱ የስራ ዘመን ማብቂያ በአንድ ወቅት አይሆንም፤

## ?፩.የቦርዱ ሥልጣንና ተግባርና

ቦርዱ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ መደበኛና የካፒታል በጀት ያፀድቃል፤

፪ የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑትን የሥራ ኃላፊዎች ሹመት እና ስንብት ከቦርድ አስተያየት ጋር ለከንቲባው አቅርቦ ያጸድቃል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫ የኮርፖሬሽኑ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይልና ደመወዝ ፣የሙያ ክፍያ እና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ መርምሮ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፤

፬ መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸዉ የተገነቡ የክላስተር ልማት ማዕከላት ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በኪራይ የሚተላለፍበትን አሰራር ያጸድቃል፤ በአግባቡ መከናወኑን ይከታተልል፤ ይደግፋል፤

4. The terms of service of board members will be five years; the board members may be assigned or elected for anoter five years after the complesion of the intial term.

5. In order to maintain the continuity of the activities of the board, the term of office of its members shall not expire at the same time.

## 11. Power and Duties of the Board

The board, being accountable to theBureau, shall have the following powers and duties:

1. approve the strategic and annual plan as well as the recurrent and capital budget of the corporation;
2. present and cause the approval of the appointment and dismissal of heads, that are accountable to the general manager of the corporation, to the mayor together with the opinion of the board; implement the same up on approval;
3. examine, approve and adjust the organizational structure, human resource, salary and profesinal payment of the corporation;
4. approve the arrangement of transferring the cluster development centers built with complete infrastructure to the small and medium manufacturing industries through lease; follow-up its proper implementation; support the same;

፭ የክላስተር ማዕከላትን የኪራይ ዋጋ ይወስናል፣ ኪራዩም በአግባቡ መሰብሰቡን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮ በክላስተሮች ልማት ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጎጂ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤

፯ የኮሮፖሬሽኑ መቋቋሚያ በጀት ከአስተዳደሩ እንዲመደብ ያደርጋል፤

፰ በኮሮፖሬሽኑ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤

፱ የኮሮፖሬሽኑ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ሀሳብ ያቀርባል፤

? ለኮፕሬሽኑ ስራ የሚውል የአጭርና የረጅም ጊዜ ብድር እንዲያገኝ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይጠይቃል፣ ያፀድቃል ፣ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

?፩በኦዲተሮች የሚቀርቡ የሂሳብ ሪፖርትና መግለጫዎችን ይመረምራ፤ ያጸድቃል፣ ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል፤

5. determine the rental rate of cluster centers; follow-up the proper collection of the rent; control the same;

6. support and coordinate the rehabilitation activities of those directly or indirectly affected segments of the community, due to clusters development, with the concerned organs;

7. cause the allocation of budget for the establishment of the corporation by the administration;

8. approve sales of fixed assets that have no significant impact to the existence of the corporation;

9. propose to the supervising authority the increase or decrease of the capital of the corporation;

10. request, as per to the law, for the acquisition of short and long term loans to be used for the activities of the corporation; approve and follow-up the implementation of the same;

11. examine and approve the financial reports and statements presented by auditors; take proper measures;

፲፪ የኮሮፖሬሽኑ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ይገመግማል፡፡

12. appraise the performance report of the corporation;

## ፲፪. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

፩ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ቢያንስ ሶስት አባላት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ የቦርዱ ሰብሳቢ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫ የቦርዱ የስብሰባ አጀንዳ በቅድሚያ ለቦርዱ አባላት እንዲደረስ ይደረጋል፡፡

፬ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፭ ቦርዱ በድምጽ ብልጫ ይወስናል፣ድምጽ እኩል ለእኩል በሚሆንበት ጊዜ የቦርዱ ሰበሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፮ ቦርዱ ከኮሮፖሬሽኑ ሠራተኛ መካከል ፀሐፊ መርጦ ይመድባል፡፡

፯ የኮሮፖሬሽኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው በቦርዱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ ይችላል፡፡

## 12 . procedure of the meeting of the board

1. The board shall meet atleast once a month.
2. The board chair person may arrange extra ordinary meeting when there is sense of urgency or at arequest of its chair person or one third of its voting members.
3. The agenda of a board meeting shall, in advance, be communicated to the board members.
4. There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting.
5. The board shall take decision by majority vote, in case of a tie, the chairman shall have a casting vote.
6. The board shall select and assign a secretary from among the employees of the corporation.
7. The General manager of the corporation may attend meetings of the board without having the right to vote.

፰ ቦርዱ በየስብሰባው በተገኙት አባላት የሚፈረም ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

፱ ቦርዱ የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ?፫. የቦርድ አባላት ተጠያቂነት

፩ የቦርድ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጣቸውን ተግባር በጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፡፡

፪ አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ምክንያት በኮሮፖሬሽኑ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተገለፀው ቢኖርም ቦርዱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ውሳኔው ትክክል አይደለም ብሎ በድምጽ የተለየ የቦርድ አባል ውሳኔው በድርጅቱ ላይ ለሚያስከትለው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ?፬. የኮሮፖሬሽኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

የኮሮፖሬሽኑ ዋና ስራ አስኪያጅ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩ የኮሮፖሬሽኑ የማስፈጸሚያ መመሪያዎች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

8. The board shall keep minutes for every meeting, which shall be signed by the attending members present.
9. The board shall draw its own rules of procedure.

## 13. Liability of Board Members

1. The members of the board Shall carry out their duties assigned under this proclamation with due care.
2. The members shall be jointly and severally liable to the corporation for the damage caused by their failure to properly carry out their duties.
3. Not with standing sub-article (2) of this Article, a board member shall not be liable where he has dissented from the decision of the board which caused damage.

## 14. Power and Duties of the General Manager

The general manager of the corporation shall have the following powers and duties:

1. prepare and present the implementation directives of the cooperation to the board; implement the same up on approval;

፪ የኮርፖሬሽኑ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ያስተባብራል፣ያስፈጽማል፣

፫ የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጅክና ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድለትም በስራ ላይ ያውላል፡፡

፬ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የፋይናንስና የቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦት የሚያገኙበትን የአሰራር ስርአት ዘርግቶ ይደግፋል፣

፭ የተሟላ መሰረተ ልማት የተዘረጋላቸው የማምረቻ፣ የመሸጫ እና የማሳያ ቦታዎችን በክላስተር ማዕከላት በመገንባት የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በኪራይ ያስተላልፋል፣ ኪራዩንም ይሰበስባል፣ ያስተዳድራል።

፮ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከአገር ዉስጥ ምርት የጥሬ ዕቃ እና ለምርታቸዉም የዉጪ ገበያ ትስስር የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ይደግፋል፡፡

፯ ለኮርፖሬሽኑ ክላስተር ልማት የሚያስፈልገውን የአጭርና የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ብድር ያፈላልጋል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ ይበደራል፣ የተበደረውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ እንዲመለስ ያደርጋል፤

2. lead, manage and coordinate the corporation superiorly; execute the same;

3. prepare the strategic and annual work plan and budget of the corporation; implement it upon approval;

4. establish a method for small and medium manufacturing industries to obtain financial and technological input supply and support the same;

5. build manufacturing, selling and display places which have complete infrastructural facilities in the cluster centers and transfer it through lease to small and medium manufacturing industries; collect the rent; and administer the same;

6. provide support for small and medium manufacturing industries so as to access them local row material and export market linkage through establishing procedural system;

7. find short and long term finance loans that are needed for the cluster development of the corporation; handle the loan upon the approval of the board; cause the repayment of the loan within the set period of time;

፰ የኮሮፖሬሽኑን ሂሳቦች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ በቦርድ ውሳኔ የሚከፈተውን የኮርፖሬሽኑን የባንክ ሂሳብ ከሂሳብ ባለሙያ ጋር በጣምራ ያንቀሳቅሳል፤

፱ የኮሮፖሬሽኑን ሰራተኞች በህግ መሰረት ይቀጥራል፤ያስተዳድራ፤ያሰናብታል፤

? ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉት ግንኙነት ኮሮፖሬሽኑን ይወክላል፤

?፩ቦርዱን በማስፈቀድ በኮሮፖሬሽኑ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን የኮሮፖሬሽኑ ቋሚ ንብረቶች እንዲሸጥ ያደርጋል፤

?፪ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው መጠን ስልጣኑን ለኮሮፖሬሽኑ የስራ ሀላፊዎች በውክልና ይሰጣል፤

?፫ በስራው ሂደት ላይ የሚመክርና በስራ ግምገማዎች በእቅዶችና ውሳኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ይመራል፤

?፬ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል ፤ ውሳኔዎችን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤

?፭. <u>የዋናው ሥራ አስኪያጅ ኃላፊነትና ተጠያቂነት</u>

??? ? ? ??? ?? ???? ?? ??? ?? ?? ?????? ???? ? ? ?? ?ኮሮፖሬሽኑ ?? ?? ???? ??? ??? ???? ????

8. cause the proper handling of the accounts of the corporation; manage the bank account of the corporation which is opened by the decision of the board together with an accountant;

9. hire, manage and dismiss employees of the corporation in accordance with the applicable law;

10. represent the corporation in its dealings with third parties;

11. cause the sale of fixed assets of the corporation that do not have a significant impact on the existence of the corporation upon the permission of the board;

12. delegate his power to other heads of the corporation as may be found necessary;

13. establish and lead a management committee that consults on the process of the work and discuss the work appraisals, plans and decisions;

14. carry out other activities delegated by the board; execute decisions and cause the execution of the same;

**15. <u>Responsibility and Liability of the general manager</u>**

The general manager shall be liable in accordance with the law, for damage he causes on the corporation through negligence or intentionally.

## ክፍል ሦስት
## ካፒታል፤ የበጀት ዓመት፣ የበጀት ምንጭና ኃላፊነት

**?፮.ካፒታል**

የኮርፖሬሽኑ ?? ? ? ? ?? ? ? ? ? 200,000,000.00 (? ?? ? ? ? ? ? ? ? ?) ? ? ? ??? ? ?? ? ? 157,000.000.00 (? ? ? ? ? ?? ? ??? ? ? ? ? ? ?) ? ? ? ???? ? ??? ?? ?? ? ? ? ? ? ? ? ? ? ??

**?፯.የበጀት ዓመት**

የኮርፖሬሽኑ ???? ?? ? ?? ???? ???? ?? ? ? ? ? ? ??

**?፰.የበጀት ምንጭ**

የኮርፖሬሽኑ የበጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩ በአስተዳደሩ የሚመደብ የማቋቋሚያ ካፒታል፤

፪ ኮርፖሬሽኑ ከሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ከሚሰበሰብ ገቢ፤ እና

፫ ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ፡፡

**?፱.ስለ መጠባበቂያ ሂሳቦች እና አጠቃቀም**

፩ ኮርፖሬሽኑ ህጋዊ የሆነ መጠባበቂያ ሂሳብ ይይዛል፡፡

፪ በሌላ ህግ በተለየ ሁኔታ የተወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮርፖሬሽኑ ከተጣራ ትርፍ ላይ ፭ በሙቶ በየዓመቱ እያነሳ ህጋዊ መጠባበቂያው ሂሳብ የኮርፖሬሽኑ ካፒታል ፳ በሙቶ እስከሚሆን ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሳቡ ያስገባል፡፡

## PART THREE
## CAPITAL,FINANCIAL YEAR, BUDGET SOURCE AND LIABLITY

**16. Capital**

The authorized capital of the corporation shall be Birr 200,000,000.00 (Two hundered million Birr) out of which 157,000,000.00 ( one hundered fivety seven millon Birr) shall be pre-paid in cash and in kind.

**17. Fiscal period**

Fiscal period of the corporation shall be that of government budget year.

**18. Budget source**

The following shall be the budget sources of the corporation:

1. An establishment capital allocated by the administration;
2. Revenue collected from the various services provided by the orporation; and
3. Revenue obtained from other legal sources.

**19. Reserve funds and their utilization**

1. The corporation shall establish and maintain a legal reserve fund.
2. Without prejudice to the provisions of other laws providing otherwise, the corporation shall annually transfer 5% of its net profits to the legal reserve fund until such reserve fund equals 20% of the capital of the coroporation.

፫ ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳቡ፡-

ሀ. ኪሳራን ለመሸፈን

ለ.ያልታሰቡ ወጪዎችንና እዳዎችን ለመሸፈን ሊውል ይችላል፡፡

3. The legal reserve fund may be utilized for covering
   a). losses; and
   b).unforeseeable expenses and liabilities.

**?. <u>የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ</u>**

ኮርፖሬሽኑ ሂሳብ ዓመቱ ከተፈፀመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት ወራት ውስጥ የመንግስቱን የትርፍ ድርሻ ለመንግስት ፈሰስ ያደርጋል፡፡

**20. <u>Dividend of the government</u>**

The Dividend of the government shall be transferred within seven months from the end of finical period.

**?፩.<u>ስለ ግዢና የፋይናንስ ሥርዓት</u>**

የኮርፖሬሽኑ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት በመንግስት የልማት ድርጅቶች የግዥና የፋይናንስ ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

**21. <u>Procurement and Financial system</u>**

The procurement and financial system of the corporation shall be governed by the procurement and financial system of public enterprises.

**?፪.<u>ኃላፊነት</u>**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**22. <u>Liability</u>**

The Corporation may not be liable beyond its total asset.

**፳፫. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**23. <u>Duration of the Corporation</u>**

Duration of the Corporation shall be unlimited.

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ስለ ሂሳብ መዛግብት እና ምርመራ</u>

**፳፬. <u>ስለ ሂሳብ መዛግብት</u>**

፩ ኮርፖሬሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

## <u>PART FOUR</u>
## <u>BOOKS OF ACCUNTES AND AUDITING</u>

**24. <u>Books of Accounts</u>**

1. The corporation shall retain complete and accurate book of accounts.

፪ የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ሌሎች ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**፳፭ <u>ሂሳብ ስለ መዝጋት</u>**

ኮርፖሬሽኑ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሂሳቡን ይዘጋል፡፡ ዓመታዊ ሂሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መዘጋት አለበት፡፡

**፳፮ <u>ሂሳብ የማስመርመር ግዴታ</u>**

የኮርፖሬሽኑን ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፳፯ <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም የሚመለከተው አካል ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚደረገው ማንኛውም ተግባር ትብብር እንዲያደርግ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፰ <u>ስለ ሌሎች ህግ ተፈፃሚነት</u>**

በዚህ አዋጅ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2. The book of accounts and financial documents of the corporation shall be inspected annually by the administration general Auditor or auditors assigned by him.

**25. <u>Completion of Book of Accounts</u>**

The Corporation's books of accounts shall be completed yearly; annual book account shall be complete within three months from the lapse of the budget year.

**26. <u>Obligation to examine Books of Account</u>**

Who ever received money or property of the corporation draws money, paid or any person responsible for books of account shall be duty bound to let the examination of books of accounts and to submit appropriate documents required.

**<u>PART FIVE</u>**

**<u>MISCELLANEOUS PROVIISION</u>**

**27. <u>Duty to cooperate</u>**

Any concerned organ shall have the duty to cooperate in an activity to implement this proclamation whenever he is requested to do so.

**28. <u>Applicability of other Laws</u>**

Uatters those are not provided by this proclamation shall be regulated by the public Enterprises proclamation no. 25/1992.

## ፳፱ ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ላይ በተመለከቱ ጉዳዮች ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፴ ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩ የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

፪ ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም ቦርዱ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፴፩ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ድሬዳዋ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም**

**ኢብራሂም ዑስማን**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

## 29. Inapplicable Laws

Any proclamation, regulation, directives or customery practice which are inconsistent with this proclamation shall no effect on maters provided for in this proclamation.

## 30. Power to issue Regulation and Directives

1. The cabinet of the Dire Dawa Administration may issue regulations for the implementation of this proclamation.
2. The board may issue directive for the implementation of this proclamation and regulations issued there after.

## 31. Effective Date

This proclamation shall come in to force up on the date of publication in the Dire Negarit Gazeta.

**Done at Dire Dawa this 2ed day of November 2017**

**Ibrahim Osman**

**Mayor of Dire DAwa Administration**